ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

Tel 202291 4217 mailling address: P.O.Box 73337, Washington Dc 20011

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓም የተላለፈ ሐተታ

## ልፅደቅ ብየ ባዝላት ትንጠልጥላ ቀረች !

በተለያዩ አጋጣሚዎች ፤ ከመንግሥት ሥልጣን ላይ የሚኮፈሱ ቡድኖች ሁሉ፤ ለአገዛዝ ጭካኒያቸው ወደር አይገኝለትም። በሁሉም መስፈርት ሲለኩ፤ በጭካኒያቸው ጽንፈኞች ናቸው። ትንሽም እንኳን ቢሆን ለሕዝብና ለመጭው ትውልድ የሚተርፍ መልካም ትውስታና ትዝታ ማትርፍ የሚያስችል እውቀት አይኖራቸውም ። በዚህ ምክንያት የሕዝቡ ጥላቻና ተቃውሞ ከመጠን በላይ ይሆንና ዐይናችሁን ለዐፈር ብሎ የረግማቸዋል። መልካም ታሪክ ሰርተው ስለማያልፉ፤ በጎ ቅሪት አኖራቸውም ። ሀገሪቱንም እንደ ባቢሎን ግንብ ፈራርሳ እንድትቀር ይመርጣሉ። የዜጎቿንም ታሪክ ፤ እንደ ሎጥ ሚስት የጨው ሀውልት አድርገውት ያልፋሉ። ለነገ ታሪክም ሆነ ለተተኪው ትውልድ ስለማይጨነቁ፤ ሀገርና ትውልድን መና አድርገውት ያልፋሉ። ለወደፊቱ ፤ " የኋላ ልጅ ይጨነቅበት " የሚል ፈሊጥ፤ ማሳፈሪያ ጥቅስ ተናግረው ይጠፋሉ።

በዚህ ምክንያት ፤የሚገዙት ሕዝብ በሙሉ ይንገፈገፍባቸዋል ። ይፈራቸዋል። ይጠላቸዋል ። ይቃወማቸዋል ። ከአገዛዝ ቀንበራቸው ለመላቀቅ ሲል ፤ ሕዝብ፤ የማያደርገው የተጋድሎ ጥረት አይኖረውም ። በወቅቱ ካለው አገዛዝ ለመገላገል ሲል፤ አዲስ የሚመጣውንም፤ " ዕባብ ያየ በልጥ በረየ ! " ሆኖበት በጥርጣሬ ማየቱን ይቀጥላል ። የቀረውም ዜጋ በበኩሉ፤ አዲስ የሚመጣው ምናልባት ካለፈው የተሻለ ይሆን ይሆናል ከሚል የጭንቀት ተስፋ፤ ጊዜ እንስጠው ብሎ ጓጉቶ ይጠብቃል ። በአዲስ ተስፋ፤ ለአዲስ መጭው፤ በሙሉም ባይሆን በከፊሉ ይተባባረዋል። የደርግ አገዛዝ ስላንገፈገፈው ነበር፤ ወያኔን በራፉን ከፍቶ ሊያስገበው የሞከረው። የተዝናጋውም፤ ከደርግ የተሻለ ይመጣ ይሆናል በሚል በጎ ምኞት፤ በተስፋ ተታለለ እንጅ፤ ወያኔን ወድዶና አምኖ አልነበረም። ይኸን በማድረጉ አይፈረድበትም። ምክንያቱም፤ ምንም ቢሆን፤ የዜጎቹን ሬሳ ከሚሸጥ መንግሥት የከፋ ሌላ መንግሥት ይመጣ ይሆናል ብሎ ስላላሰበ ነበር። የሆነው ግን፤ የዜጎችን ሬሳ ከመሸጥ በላይ፤ ሀገር የሚሸጡ ከሃዲዎች መምጣታቸው ነው።

ያም ሆኖ ግን፤ እዚህ ላይ ፤ የሦስት ከተሞች ተጋድሎን፤ በታሪክ ሳይጠቀስ ማለፍ አይቻልም ። እነርሱም ዳባት፤ ደብረታቦርና አምቦ ከተሞች ነበሩ። ወራሪውን የወያኔ ጦር በጀግንነት ተጋትረው እረፍርፈዉታል ። የወያኔ ጦር የደብረታቦር ከተማን ከተማን ፤ በቀላሉ አልያዛትም። ሕዝቡ 72 ሰዓት ተዋግቷቸዋል ። ወያኔ አዲስ አበባ ሊገባ የቻለውም ፤ በእነኝህ ከተሞች ጀግኖችና በኢሕአፓ ቆራጥ ታጋዮች ሬሳ ተረማምዶ ነበር ! ምንም ጊዜ ቢሆን፤ ኢትዮጵያ ልትፈርስ የምትችለው ፤ የጀግኖች ልጆቿ ሬሳ ተረፍርፎ

ካለቀ ባኋላ መሆኑ ባላንጣዎቿ ሊገነዘቡት ይገባቸው ነበር ! ይኽን ታሪካዊ ሃቅ ለማስተዋል ግን አስተዋይ ኅሊና አልነበራቸውም ።

" ዳመናው ሲደምን ፤ ሲደማምን ፤ ይውረዛል ገደል ፤ "

ይዘገያል እንጅ መመለሱ አይቀርም ፤ የሠማዕት በደል ።

ተብሎ የተዜመው በከንቱ አልነበረም።

ደርግና ግብረ አበሮቹ ግን ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ክደውና አጋልጠው ሀገሪቱንም ለከፋፋዮች አስረክበዋት ሸሹ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ የወያኔን በህርይና ዐላማ በሚገባ ሳይረዳ በመቅረቱም ጉድ ሆነ ። አሁን ታዲያ " ዕፀድቅ ብየ ባዝላት ፤ ተንጠልጥላ ቀረች ! " እያለ የሀዘን ቁጭት ይቆጫል ። እረ አይሆንም ! ወያኔን አትመኑ ! ብለው ያስጠነቀቁ ክፍሎችም ፤ "ዐይናችሁን ለዐፈር ! " ተባሉ። ሌላው ሁሉ ታሪክ ሆኖ ቀረ ! ምሾ እየደረደሩ ደረት መምታት ሆኖ ቀረ ! የሕዝብ ቋሚ ሮሮና ጮኸት ግን ከንቱ ሆኖ የሚቀር አይደለም ። ታሪካዊ ሀቅ በመሆኑ ፤ የሚሆነው ይሆናል ። የማይሆነው አይሆንም ። የሚሆነውን ለማምጣት ግን የሚሆነውን እየሰሩ መሥዋዕት መክፍልን ይጠይቃል ። "ያለ መሥዋዕት ስርየት የለምና ! " በአሁኑ ሰዓት፤ አይቀሬውን መሥዋዕት በመራራ ፅዋ የሚጎነጩ በየቦታው ተፈጥረዋል። የነርሱ ደም መና ሆኖ አይቀርም ! ባዕዳኑ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ የዳጎለ ደም እጃቸውን እንዳይነከሩ እናሳስባለን !

ወያኔዎች እምኒልክ ግቢ ለመድረስ፤ " ስድሳ ሽ ወጣት ገብረናል ። " ቢሉም፤ ሀገሩን ከመከፋፈል ለማደን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ዕጥፍ ድርብ መሥዋዕት ለመክፈል የተዘጋጀ መሆንን ግን ፤ ዕነርሱ አልተገነዘቡትም ። መጀመሪያ ፤ ሀገሩን ከመከፋፈል አድኖ ነው፤ ስለ መንግሥት ሥልጣን አያያዝ ፤ ስለ ዴሞክራሲና ሀገመንግሥት፤ ማሰብ የሚቻለው ። የሀገር ሉዋላዊነትና ሕልውና ፤ የሕዝብ አንድነትና ልዕልና ሳይኖርና ሳይረገገጥ ስሌላው ማሰብ ፤ ትጥቅ አስፈች ፈሊጥ ነው ። ሀገርና ሕዝብ ከሌሉ፤ " ከባል በፊት ልጅ የስጥሽ " የሚል ምኞት ብቻ ሆኖ ነው የሚቀረው ።

ነገር ግን ፤ ሕዝባችን ፤ አንድ መሠረታዊ ጉዳይ ሳይገነዘብ በመቅረቱ ምክንያት፤አሁንም እንደ ትላንቱ፤ በአዲስ መጭው አገዛዝ ይታለላል ። አዲስ መጭውም ካለፈው አገዛዝ በበለጠ ጭካኔ እያንቀጠቀጠ ይገዛዋል ። ምንም ቢሆን፤ ካለፈው አገዛዝ የከፋ አገዛዝ ሊመጣ አይችልም ከሚል ምኞት፤ አዲሱን አባገነን " ጊዜ የሰጠው " ያሉ ብዙዎች ነበሩ ። አሁን ግን "ምነው አፋችን በዘጋው " እያሉ፤ ፀፀቱ እንደ እግር እሳት ያቃጥላቸዋል ። " አንድ ቀን ቢስቱ፤ ዐመት ይፀፀቱ " ሆነና ፤ "ወያኔን ጊዜ እንስጠው" ሲሉ የነበሩ ሁሉ፤ ዛሬ፤ "ዕጸድቅ ብየ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች ! " ብለው ፤ የወያኔን ውድቀት ይመኛሉ። ምኞታቸውን ዕውን ለማድረግ ግን ተጨባጭ ርምጃ ሲወስዱ አይታዩም። ምኞትን ወደ ተግባር መለወጥ ካልተቻለ ደግሞ ፤ ትርፉ፤ በዕርጎ ባኅር ከመዋኘት ያለፈ ውጤት አያስገኝም ።

ሁሉንም አምባገነን አገዛዞች፤ በጋራ የሚያስፈርጃቸው ጉዳይ ቢኖር፤ ሥልጣን ወዳዶች እንጅ ሕዝብና ሀገር አፍቃሪዎች አለመሆናቸው ነው። በተለያየ የታሪክ አጋጣሚ፤ ተመሳሳይ መፈክር እያመጡ፤ ሕዝብን እየታለሉ የመጡ ፀረ- ሕዝብና ፀረ- ሀገር የሆኑ አምባገነኖች ነበሩ ። ናዚዎች ወደ ሥልጣን ሲወጡ፤

" ጀርመን መጀመሪያ " (German First ! ) ብለው ነበር የመጡት ። የፋሽስቱ አለቃ ሙሶሊኒም፤ ኢጣሊያ ወደ ፊት (Andatto Italiana ! ) ብሎ ነበር የመጣው። በእኛም ሀገር ፤ ደርጎቹ ፤ ኢትዮጵያ ትቅደም ብለው ነበር ሥልጣን ላይ የወጡት። የሆነው ግን ፤ ሀገሪቱን ማስቀደሙ ቀርቶ፤ ጨዋሬታውን እንኳ ማትረፍ ሳይችሉ ቀርተው፤ ለሀገር ከፋፋዮቹ ወያኔወች አሳልፈው ሰጥተው ነው የ ሸሹት !

ታላቂቷ ሀገራችን ፤ ትንሽ ጭቅላትና ንዑሳን ስብዕና ባላቸው ግለሰቦች እጅ በመውደቋ ምክንያት አሁን ከገባችበት አዘቅጥ ለመውደቅ ቻለች ። ኢትዮጵያን ያህል ታሪካዊ ሀገርና ታላቅ ሕዝቧን ለመምራትና ለማገልገል፤ ታላቅ አዕምሮና ከፍተኛ ስብዕናን ተጎናፅፎ መገኘትን ይጠይቃል ። እስካሁን የነበሩትና አሁንም ያሉት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመምራት ቀርቶ፤ ለማገልገልም እንኳ በዕጩነት ለመሰለፍ ብቃት እንዳልነበራቸው በትግባር አስመስክረዋል ።

የሀገራችን አምባገንን አገዛዝ አራማጆች ሁሉ፤ሀገር ወዳድ ለመምሰል፤ በማር የተቀባ( Sugar Coated ) መፈክር እያሰሙ፤ ጥቂት ምዕራፍ እንኳን ሊያራምዳቸው የማይችል ፤ ፕሮፓጋንዳ ሲያሰሙ ቆይተው፤ የውሃ ሽታ እየሆኑ አልፈዋል ። የሕዝብን አዕምሮና ልብ ለማግኘት ፤ በሀቅ ላይ የተመሠረተና የማይናወጥ መርኅን የተላበሰ ተግባር ማሳየት አስፈላጊ ነው ። ይኽ በሌለበት ሁኔታ፤ ሕዝብ ማገለግልም ሆነ ሀገር ማስተዳደር አይቻልም። የሕዝብ ሙሉ ፈቃድና ትብብር ከሌለ ፤ እንምራ ብለው የሚመጡ ቡድኖቹም ሆኑ ግለሰቦች ሊሆን የሚችሉት አምባገነን አጋዛዝ አራማጆች ብቻ ሆኖ መቅረት ነው። የዚህ ውጤት ደግሞ፤ ያው ዞሮ-ዞሮ፤ የሀገር ጥፋት፤ የሕዝብ ውድመትና የትውልድ መና ከመሆን በቀር ሌላ ፋይዳ አያመጣም ። እስካሁን የታየውም ይኸው ነበር።

ለአለፉት ግማሽ ምዕተ- ዐመት በሀገራችን የታየው የፖለቲካ ሂደት፤ ሕዝቡ የጓጓለትን ውጤት ሊያስመዘግብ ያልቻለበትን ምክንያት በሚገባ ተረድቶ መገኘት ፤ የወደፊቱን ራዕይ አሻግሮ ለማየት የሚረዳ ይመስለናል። ለነገዋ ኢትዮጵያ የነገ ራዕይ ይስፈልጋታል ። የምንሄደበት አቅጣጫም ሆነ ወደፊት ልንደርስበት ያሰብነውን ግብ ለማወቅ የምንችለው፤ እስካሁን የተጓዝንበትን ጎዳና በሚገባ መርምሮና ገምግሞ በትክክል መረዳት ሲቻል ይሆናል ። ይኽንን ለማድረግ ደግሞ፤ ድፍረትንና ሀቅን ተመርኩዞ መገኘትን ይጣይቃል ። ድፍረትን ከሃቅ ጋር አቅናጅቶ መገኘት፤ ማንንም ሊያስፈራና ሊያሸማቅቅ አይችልም። ታሪክንና ሕዝብን በድፍረት መቋቋም የሚቻለው፤ ዕውነቱን ይዞ ሲገኙ እንደሆነ እናምንበታለን ።

ዐላማችን፤ በአለፉት ሰዎች ላይ አቃቂር በማውጣት ላይ ብቻ ማተኩር ሳይሆን፤ አሁን ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በሚገባ መርምሮ፤ ወደፊት መሆን የሚችለውንና የሚገባውን፤ ብሎም ለሀገርን ለሕዝብ ሊጠቅም የሚችለውን ሃሳብ ነድፎ ማሳየት ነው።ንድፈ-ኃሳብን፤ ከሀገሪቱ ተጫባጭ ሁኔታ ጋር እያዛመዱ መራመድ፤የሕዝብን ተቀባይነትንና ትብብርን ያተርፋል። የሕዝብን ሙሉ ትብብር ማገኘት ደግሞ፤ የታሰበውን ግብ ለመምታት ያስችላል። ያልተጠበቀ ስኅተትንም ከመስራት ያድናል ። ይኽንን ማሳየት ከተቻለ፤የሞራል ኃላፊነትን ለመሸከም የሚያስችል ብቃት ሊመጣ ይችላል ብለን አናስባለን። የሞራል ኃላፊነትን የተሸከመ ሁሉ፤ የሞራል ልዕልናውንም ደርቦ ለመሸከም አቅም ይኖረዋል ።የሕዝቡም ሙሉ ትብበር አይነፈገውም ። በራስ መተማመንም ሊመጣ ይችላል። በራሱ የሚተማመን ሕዝብና መሪ

ደግሞ፤ የማንንም መጽዋዕት አይጥብቅም፤ አይፈልግምም። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ፤ አስታማማኝ የሆነ የሀገር ሉዋላዊነትን ማስረገጥ ነው ። አስተማማኝ የሀገር ሉዓላዊነት ከተረጋገጠ ፤ የዚያችን ሀገር ብሄራዊ ነፃነትና ዳር -ድንበር ማንም ሊደፍረው አይችልም። የዛሪይቱ ኢትዮጵያ ፤ ለዚህ አልታደለችም ።

አሁን ያለው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለሚከታተለው፤ በተመሰቃቀለ የፖለቲካ መተረማመስ ሂደት ውስጥ እንደወደቀ በግልፅ ያየዋል ። የኃይል አሰላለፉም ፤ አቅጣጭ -ቢስ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፤ የተበታተነና፤ የተመሰቃቀለም ሆኗል ። ተቀራራቢ የሆነ አቅጣጭ የሌላው መሆኑን በተግባር እያሳየ ይተረማመሳል ። በመበታተን ላይ ለምትገኝ ሀገር፤ የተዋሃደና የተበባረ ትግል ማካሄድ ሲገባ፤ሁሉም በየአቅጣጫው ተበታትኖ የየራሱን የፖለቲካ ድንኪራ ይረግጣል ።አንድ ላይ ሆነናል የሚሉትም ቢሆኑ ሚዛናቸውን መጠበቅ እየተሳናቸው የሚዛኑን ጅዋጅዌ ( Pendulum ) ማረጋጋት ትስኖቸዋል ። በመስከረም ወር የጋብቻ ውል ተፈራርመው፤ ኅዳር ሳይታጠን ሰማኒያቸውን ይቀድዳሉ ። ከዚያ በኋላ አንዱ በሌላው ላይ የጭቃ ጅራፉን እያወናጨውፈ፤ እኔ ከደሙ ንፁሁ ነኝ ለማለት ይጣጣራል ። ወያኔም " ዕሳትና ገለባ" ያድርጋችሁ እያለች፤የሽሙጥ ፈገግታዋን ታሳያለች። አንዳንዱም፤ "ከላይ ነው ጥመቱ" እያለ፤ ከላይ ከኢትዮጵያ አምላክ ፤ እርግማን እንደመጣበት ይቆጥረዋል ። ታስፋ መቁረጥን፤ በሃሳባዊነት እንክብል እየዋጡ መብተክተክ ፤ ምክንያታዊ ስለማያደርግ፤ አምክንዮ (Logic ) በጎደለው " ትንታኔና " መግለጫ ለመስጠት ሁሉም በየፊናው ይሯሯጣል ። ዕርግጥ ሀገሪቱን ከዘረኞች መንጋጋ ለማላቀቅ፤ በግድ ተባብሮ ከመነሳት በስተቀር ሌላ አምራጭ እንደሌለ ሁሉ የተረዳው ቢመስልም፤ በተግባር ለመትርጉም ግን አልቻለም።

እስካሁን ግን ተግባራዊ ያልሆነበት ምክንያት፤ በመጠኑ ቢሆን በላይኛው አንቀፅ ለመግለፅ ተሞክሯል ። ምን መደረግ አለበት ለሚለው ጥያቄ፤ የሚመለከተው ሁሉ እንዲያስብበት ከማሳሰብ በስተቀር፤ ምንም ማለትና ማድረግ አይቻልም ።ይኽ ማለት ግን፤ " እኛ የድርሻችንን ተወጥተናል፤ለቀረው፤ የቀረው ያስብበት " ማለት አይደለም። አቅማችንን ከሁኔታው ጋር እያገናዘብን የተቻለንን ሁሉ ከማድረግ አንቆጠብም። " ልፅድቅ ብየ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች " የሚሉ ወገኖቻችን እናንተው እንደሰቀላችኋት ወያኔን እናንተው ብቻ አውርዷት አናላቸውም። አንቀልባውን ሲቀድዱ እንተባበራቸዋልን ! ይህንን ዘረኛ አጋዛዝ ለማውረድ ቢሚደረገው ትግል ሁሉ ግምባር -ቀደም ሚና ከመጫውት አንቆጠብም።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !